የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 13 እና 14

1. ስለ ምሴተ ሐሙስ ሐሰት የሆነው የቱ ነው?
ሀ. ጌታ ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው ስላወቀ እንደ ሌሎች ሐዋርያት እግሩን አላጠበውም
ለ. ለሌሎች ሐዋርያት የሥጋ ወደሙን ሥርዓት ሰርቶ ሲሰጥ ለእርሱ ከተባረከው ኅብስት አልሰጠውም
ሐ. ይሁዳ አሳልፎ የሰጠው በገዛ ፍቃዱ ሳይሆን ትንቢት ስለተነገረበት ምንም ማድረግ ስለማይችል ነው
መ. ሁሉም

2. ቅዱስ ጴጥሮስ በንስሐ ያዘነው ሐዘን ከመጽሐፍ ቅዱስ አባቶች የማንን ይመስላል?
ሀ) ንጉሥ ዳዊት ለ) ይሁዳ ሐ) አዳም መ) ሀ እና ሐ

3. ጴጥሮስ በካህናት አለቃ ቅጽር ተቀምጦ ሳለ ብላቴናዋ የክርስቶስ ተከታይ መሆኑን በምን አወቀች?
ሀ) በአለባበሱ ለ) በአነጋገሩ ሐ) ሐዋርያ መሆኑን ስለመሰከረ መ) ሀ እና ለ

4. "እረኛውን እገድለዋለሁ፣ በጎቹም ይበተናሉ "
የሚለውን ትንቢት የተናገረው ማነው?
ሀ) ኢሳይያስ ለ) ዘካርያስ ሐ) አሞጽ መ)
ንጉሥ ዳዊት

5. ማርያም እንተ ዕፍረት (ባለ ሽቱዋ ማርያም) በጌታ
ራስ ላይ ሽቱ ያፈሰሰችው በየት ነበር?
ሀ) በቢታንያ ለ) በስምዖን ዘለምጽ ቤት
ሐ) በጥብርያዶስ ባሕር ዳርቻ መ) ሀ እና ለ

6. ጌታ ወደ ጌቴሴማኒ ሊጸልይ በወጣ ጊዜ ይዞአቸው
ከሄደው ሐዋርያት መካከል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ያዕቆብ የጌታ ወንድም ለ) ያዕቆብ ወልደ
ዘብዴዎስ ሐ) ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ
መ) ሀ እና ሐ

7. ይሁዳ ከሊቀ ካህናት ጋር ጌታን አሳልፎ ሊሰጥ
የተስማማው መቼ ነበር?
ሀ) በዕለተ ማግሰኞ ለ)በዕለተ ሰኞ ሐ) በዕለተ
ረቡዕ መ) በዕለተ ሐሙስ

8. "......እንባቢው ያስተውል..." ብሎ የተናገረ ነቢይ ማነው?
ሀ) ዳዊት ለ) ዳንኤል ሐ) ኢሳይያስ መ) ሁሉም

9. ጌታ ስለ ምጽአቱ ሲናገር" ወልድም ቢሆን አያውቃትም" ማለቱ ምንን ያጠይቃል?
ሀ) ወልድ የተባለ አዳምን ይዞ የሰው ልጅ አያውቃትም ሲል ለ) ከኛ ፍጹም ስጋ መንሳቱን ሲያጠይቅ ሐ) ከኛ የነሳው ስጋ አላውቂ መሆኑን ሲገልጥ ነው መ) ሁሉም

10. ምስጢረ ቁርባን ስለምን በመብል እና በመጠጥ ተደረገ?
ሀ) ምግብ እና መጠጥ ከሰውነት ይዋሃዳልና ፈጽሞ እንደተዋሃደን ለማጠየቅ
ለ) መብል እና መጠጥ ያፋቅራልና እንዳፈቀረን ለማጠየቅ
ሐ) ምድራዊ ምግብ በራበን ጊዜ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን ሄደን እንደልባችን እንድንበላ
መ) ሀ እና ለ

11. ከአምስቱ አእማደ ምሥጢራት ውስጥ በምሴተ ሐሙስ የተገለጠው የቱ ነው?
ሀ) ምሥጢረ ሥላሴ ለ) ምሥጢረ ሥጋዌ ሐ) ምሥጢረ ጥምቀት መ) ምሥጢረ ቁርባን

12. ከሚከተሉት ስለ ምስጢረ ቁርባን ሐሰት የሆነው የቱ ነው?
ሀ) ጌታ ለሐዋርያት ብቻ ቁርባንን አቀበለ እንጂ ለራሱ አልተቀበለም
ለ) ይሁዳ ከዚህ ምስጢር ተካፍሏል
ሐ) ከትንሳዔ በኋላ የተፈጸመ ነው
መ) ሀ እና ሐ

13. ለሐዋርያት ጌታ በፋሲካ የሚበላበትን አዳራሽ የጠቆመው ወጣት ማን ነበር?
ሀ) ቅዱስ አግናጥዮስ ለ) ቅዱስ ማርቆስ ሐ) ቅዱስ ባስልዮስ መ) ቅዱስ ማቴዎስ

14. ስርዓተ ቁርባን ስለምን በሥንዴ እና በወይን ተደረገ?

ሀ)ጌታችን እና እመቤታችን ሲበሉ የኖሩት ሥንዴ እና ወይን በመሆኑ ፍጹም ሥጋውን ፍጹም ደሙን እንደሰጠን ለማጠየቅ
ለ) ካህኑ መልከጼዴቅ በሥንዴ እና በወይን ይሠዋ ነበርና
ሐ) ሥንዴ ሥብ ሥጋ ይመስላልና ወይንም ትኩስ ደም ይመስላልና በመሰለ ነገር ለመስጠት
መ) ሁሉም

15. ጌታችን በእለተ ሐሙስ ሊጸልይ የሄደባት ጌቴሴማኒ የምን ስፍራ ናት?
ሀ) የአትክልት ስፍራ ለ) የመቃብር ቦታ ሐ) የወይን ቦታ መ) የባሕር ዳርቻ

16. ከጌታ ደቀመዛሙርት መካከል ጌታችን ሲያዝ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ጆሮ የቆረጠው ማን ነው?
ሀ) ዮሐንስ ለ) ጴጥሮስ ሐ) ይሁዳ መ) እንድርያስ

17. ጌታችን በሊቀ ካህናቱ ግቢ ሳለ በጥፊ ከመቱት ሰዎች መካከል አንዱ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ማልኮስ ለ) ቀያፋ ሐ) መጻጉዕ መ) መልሱ የለም

18. ይሁዳ ጌታን ለሚይዙት ሰዎች የሰጣቸው ምልክት ምንድን ነበር?
ሀ) ከሁሉም ይልቅ ደም ግባት ያለውና መልከመልካሙ እርሱ ነው
ለ) የምስመው እርሱ ነው
ሐ) የምሰግድለት እርሱ ነው
መ) ለ እና ሐ

19. ጌታችን በምሴተ ሐሙስ ተሰብስበው ሳለ ስለ ይሁዳ ከተናገረው ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?
ሀ) ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር
ለ) ከእኔ ጋር እጁን ወደ ወጭቱ የሚያጠልቀው ነው
ሐ) ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮህ ሶስት ጊዜ ይክደኛል
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

20. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለዳግም ምጽአቱ በምን መስሎ ነገራቸው?
ሀ) የወይን እርሻውን ተግቶ በሚጠብቅ አትክልተኛ
ለ) በማንኛውም ሰአት ሊጮህ በሚችል ዶሮ
ሐ) የጌታን መምጣት በሚጠባበቁ የሰማይ መላእክት
መ) ቤቱን ትቶ ለአገልጋዮቹ ስራ ሰጥቶ፣ በረኛውንም እንዲተጋ አዝዞ ወደ ሩቅ ሃገር እንደሚሄድ ሰው

21. “ከሱ ጋር ቆመው ካሉት አንዱ ሾተሉን መዘዘ......ጆሮውንም ቆረጠው” በዚህ ቦታ ላይ ድርጊቱን ያደረገው ሐዋርያ ስም ያልተጠቀሰው ስለምንድን ነበር?
ሀ) ቅ.ማርቆስ መጥቀስ ስላልፈለገ
ለ) ምክንያቱ አይታወቅም
ሐ) ድርጊቱን ያደረገው ሐዋርያ ይህ ወንጌል ሲጻፍ በሕይወት ነበረና ለእርሱ ደኅንነት
መ)አድራጊው ጸሐፊው ነበርና ለሕይወቱ ሰግቶ

22. በማርቆስ ወንጌል 14፡ 51 ላይ "ዕርቃኑን በነጠላ የሸፈነ አንድ ጎልማሳም ይከተለው ነበር " የተባለው ወጣት ማን ነበር?

ሀ) ስምዖን ቀነናዊ ለ) ኒቆዲሞስ ሐ) ማርቆስ
መ) ዮሐንስ

23. ጌታ በደብረ ዘይት ባስተማረው ትምህርት ውስጥ በነቢዩ ዳንኤል የተነገረው ምልክት ምንድን ነው?
ሀ) የናቡከደነጾር ሐውልት መፍረስ
ለ) የጥፋት ርኵሰት በቤተ መቅደስ መሆን
ሐ) የተለያዩ አራዊት ሰውን መጥፋት
መ) መልሱ የለም

24. ምጽአት ምልክቶች ተብለው ከተገለጹት ውስጥ የሆነው የቱ ነው ?
ሀ) የሀሰተኛ ነቢያት መምጣት
ለ) የጦር ወሬ በየቦታው መሰማት
ሐ) ልጆች በወላጆቻቸው ላይ መነሳት
መ) ሁሉም

25. ከሚከተሉት ውስጥ ጌታችን በተያዘበት ሐሙስ ያልተከናወነው የቱ ነው ?
ሀ) የጌታችን በጥፊ መመታት
ለ) የጴጥሮስ ጌታችንን መካድ

ሐ) ከሄሮድስ ወደ ጲላጦስ መንገላታት
መ) ጌታችን ላይ ምራቅ መትፋት

26. ሊቀ ካህናት ጌታችንን "አንተ ክርስቶስ ነህን" ብሎ ሲጠይቀው ጌታችን ምን መለሰለት ?
ሀ) አዎ ለ) ዝም ነው ያለው ሐ) መጻህፍትን አንብቡ መ) አይደለሁም

27. "ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚያ አይቀርም" ስለተባለው ቃል ጌታን ከጠየቁት ሐዋርያት ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) እንድርያስ ለ) ማቴዎስ ሐ) ጴጥሮስ
መ) ዮሐንስ

28. በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ጌታችን ጸልዮ ሲመለስ ሐዋርያት ምን እያደረጉ ነበር?
ሀ)ሰይፋቸውን እየሳሉ ለ)እየጸለዩ ሐ)ተኝተው
መ)እርስ በራሳቸው እየተነጋገሩ

29. ጌታችን ስለሚመጣበት ጊዜ እና ሰዓት ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ)መላእክት ጊዜውን ያውቃሉ
ለ)ለሐዋርያት ነግሮአቸዋል
ሐ)አብ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እና መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው ሚያውቁት
መ) ነቢያት ያውቁታል

30. ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችንን ከካደ በኋላ ዶሮ ሲጮህ ምን አደረገ?
ሀ)የጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ቃል እያሰበ አለቀሰ
ለ)ታንቆ ሞተ
ሐ) ድጋሚ ወደ ሊቀካህናቱ ግቢ ገባ
መ)ሁሉም